# አገራዊ መግባባትን ያቀዳጀ የፖለቲካ ድርጅት

**መሐመድ ኑር ሁሴን**

በኢትዮጵያ የሕዝቦችን እኩልነት፣ ነፃነትና አጠቃላይ ሰብአዊ መብትን ያረጋገጠ ህገ መንግስት ስራ ላይ ከዋለ ሁለት አስርት ዓመት ተቆጥሯል፡፡ በዚህ ህገ መንግስት አማካኝነት አገሪቱ በታሪኳ አይታው የማታውቀው ዓይነት ጠንካራ መሰረት ያለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ገንብታለች፡፡

በኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን፣ የፕሬስ ነፃነትን፣ የፍትህ የበላይነትንና ሁለንተናዊ የዜጎች መብቶች ህገ መንግስታዊ ዋስትናን ተጎናፅፈዋል፡፡ ህገ መንግስቱ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በአገሪቱ የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ቁልፍ ተዋናይ እንዲሆኑ ያስቻለ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ ኃብት እኩል ተጠቃሚዎች እንዲሆኑም አድርጓል፡

ይህ ህገ መንግስት ከዘመን ዘመን እየተሻገረ ይመጣ በነበረው የፖለቲካ ጭቆና እጅግ ተማሮ በአንድ ወቅት ለመበታተን አፋፍ ላይ ደርሶ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ  አንድነቱን አጠናክሮ የጋራ አገራዊ ራእይ እንዲኖረው ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡

ለብዙ ዘመናት የኖረው የጭቆና ስርዓት ተገርስሶ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በአገራችን መተከሉ፣ የአገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦችም ያለማንም ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበትና አገራዊ ሃብትንም ፍፁም ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ሁሉም ዘንድ እንዲደርስ መደረጉ አገሪቱ ወደአዲስ ምእራፍ እንድትሸጋገር መንገዱን ጠርጓል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ዜጎች ልብ ውስጥ ጠንካራ መተማመንና አገራዊ ስሜት እንደዚሁም ብሄራዊ ባለቤትነት ተፈጥሯል፡፡

ይህ መተማመንና ብሄራዊ የአገር ስሜትም መላው ህዝብ ለዘመናት ጠፍንጎት የኖረውን ድህነት ለመዋጋት በአንድነት እንዲነሳሳ ኃይል ሆኖታል፡፡ በዚህም አማካኝነት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት አገሪቱ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የሚያስችላትን አመርቂ ጎዳና ለመያዝ በቅታለች፡፡

የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በቅርብ የሚከታተሉ አካላት እንደሚሉት በአገሪቱ በአሁኑ ወቅት የሚታየው የጋራ አገራዊ የአንድነት ስሜት፣ እድገትና ሁለንተናዊ ለውጥ መሰረቱ በሕዝቦች ቀጥታ ተሳትፎ ስራ ላይ የዋለው ህገ መንግስትና ይህንንም ተከትሎ የተመሰረተው ፌደራላዊ የፖለቲካ መዋቅር ነው፡፡

ይህ መልካም ሁኔታ የመጣው የመላው የአገሪቱ ህዝቦች ዘመናትን ያስቆጠረ ትግልን ተከትሎ ቢሆንም ይህ ህዝብ በተለያየ መልኩ ያካሄደው ትግል ለዚህ ፍሬ እንዲበቃ ከማስቻል አንፃር ግን ከማንም የላቀ መጠን ቁልፍ ሚና የተጫወተው በአሁኑ ወቅት አገሪቱን በመምራት ላይ የሚገኘው ኢህአዴግ መሆኑን ማንም ሊክደው የማይችለው እውነት ነው፡፡

በእኔእምነት ኢህአዴግ በማንምና በምንም ሊሸነፍ አይችልም ተብሎ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ይነገርለት የነበረውን የደርግ ሰራዊት ለመገርሰስ የቻለው በሳልና ውጤታማ አመራር በመስጠቱ ብቻ ሳይሆን በተግባሩ የህዝብ አመኔታንና ድጋፍን በማግኘቱ ጭምር ነው፡፡ ድርጅቱ የህዝብ አመኔታና ያላሰለሰ ድጋፍ ባያገኝ ኖሮ በወቅቱ ከአፍሪካ እጅግ ግዙፍ የነበረውን የደርግ ወታደራዊ ኃይል ማንኮታኮት ባልተቻለው ነበር፣ ዛሬ የምናያት አዲሲቷ ኢትዮጵያም እውን ባልሆነች ነበር፡፡

ይህ ድርጅት በህዝቡ የሚቸረው አመኔታና ድጋፍ ከትጥቅ ትግሉ በኋላም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ለዚህ ጉልሁ ማሳያ ድርጅቱ አገሪቱን እንዲመራ በህዝቡ ዘንድ ተከታታይ ይሁንታ ማግኘቱ ዋነኛው ነው፡፡

በህገ መንግስቱ መሰረት በአገራችን ላለፉት 20 ዓመታት አራት ያህል አገር አቀፍ ምርጫዎች ተካሂደዋል፡፡ በእነዚህ ምርጫዎችም በርካታ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች ተወዳድረዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን በተከታታይ በተካሄዱት ምርጫዎች ሁሉ ህዝቡ መንግስት ሆኖ እንዲመራው የመረጠው ኢህአዴግን ነው፡፡

ድርጅቱም ታዲያ አሁንም የተጣለበትን ህዝባዊ ኃላፊነት ለመወጣት እስከ ህይወት መስዋእትነት ድረስ በመክፈል ላይ ይገኛል፡፡ በአገራችን ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ከፍተኛ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ማህበራዊ የልማት እድገቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዚህ እድገት አማካኝነትም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዘጎች ከድህነት ወጥተዋል፡፡

የተጀመረው የልማት እድገት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ እና ከእድገቱ መላውን ዜጋ እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ የልማት ውጥኖችም በሚያመረቃ መንገድ በመካሄድ ላይ መሆናቸው የሚታይና የሚጨበጥ ሀቅ ነው፡፡

ታዲያ አገሪቱ በመላው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ውዳሴ የተቸረውን ይህንን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካ ስኬት ማስመዝገብ የቻለችው አሁንም በኢህአዴግ የአመራር ዘመን ነው፡፡

የፖለቲካና የማህበረሰብ ሳይንስ ምሁራን እንደሚሉት ማንኛውም መንግስት የሚመራውን ህዝብ ህይወት ለመለወጥ በየደረጃው ስራ ላይ የሚውልና በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ሊተገበር የሚችል ራእይ ሊኖረው ይገባል፣ ያም ሆኖ ራዕዩ እውን ይሆን ዘንድ በቅድሚያ ሊጨበጡ ከሚገባቸው ወሳኝ ግብአቶች መካከል የራዕዩን ህዝባዊነትና አመኔታ ማትረፍ ከሁሉም በላይ ቁልፉ ነው ይላሉ፡፡

ኢትዮጵያ ወደአዲስ የእድገትና ለውጥ ምእራፍ መሸጋገር የጀመረችው አገሪቱን የሚመራው መንግስት ግልፅና የላቀ የለውጥ ራዕይ በመቅረፁ፤ ይህንንም ወደተግባር ለመለወጥ ህዝባዊ አመኔታንና ይሁንታን በመቸሩም ጭምር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የሚታየው አገራዊ ለውጥ የገዢው ፓርቲ በሳል አመራርና ጥልቅ የሆነ ራዕይ ይህንንም ተከትሎ መላው ህዝብ ያሳየው እምነትና የሰጠው ያላሰለሰ ድጋፍ ያመጡት ነው፡፡

ኢህአዴግ በውስጡ ይዞ እያጎለበተው የመጣው ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ህዝባዊነት ሌላ ኃይልና ጥንካሬንም ቸሮታል፡፡ ድርጅቱ በተለያዩ ወቅቶች ያጋጠሙትን ወስጣዊ ፈተናዎች በድል በመወጣት የቆመለተን ዓላማ ይዞ መቀጠሉ የጥንካሬው ምንጭ ነው፡፡  ከዚህም ሌላ ኢህአዴግ አገሪቱን በመራባቸው ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ከአገራዊ ፖሊሲዎችና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ከተለያዩ የውጭ ኃይላት የሚቀርብበትን ተፅእኖ እየተቋቋመ፤ ለአገር ጥቅም የሚበጁ ጠንካራ የልማት አጋሮችን እያፈራ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን ለውጥ ማምጣት መቻሉም የዚሁ ጥንካሬው ማሳያ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ባለፉት ዓመታት በየደረጃው ተቀርፀው ስራ ላይ የዋሉትና ውጤት በማሳየት ላይ የሚገኙት  አገራዊ የልማት ራእዮች የገዢው ፓርቲ የአእምሮ ምጥቀት ውጤቶች ናቸው፡፡  እነዚህ አእምሮዎች ናቸው አገሪቱን ላለፉት ዓመታት የመሩት አሁንም በመምራት ላይ የሚገኙት፡፡

ከእነዚህ አእምሮዎች መካከል አገሪቱን ላለፉት ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትርነት የመሩት አቶ መለስ ዜናዊ ግንባር ቀደሙ ናቸው፡፡ እኚህ ሰው ለዛሬዋ ኢትዮጵያ እውን መሆን የነበራቸው ሚና ከማንም የላቀ ነው፡፡ ከመነሻው ጀምሮ ለተወሰኑት ለውጦች ምክንያት በሆነው ሁለንተናዊ አገራዊ ራእይ ውስጥ የመሪው መለስ ዜናዊ አሻራ በጉልህ የሚታይ መሆኑን ብዙዎች የመሰከሩት እውነት ነው፡፡

የመለስን ህልፈት ተከትሎ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ የተፈጠረው ሐዘንና ቁጭት እንደዚሁም ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የተደመጡት ምላሾች መለሰ ለአገራቸው ብሎም ለመላው ዓለም ላበረከቱት የላቀ አስተዋፅኦ የተሰጠ ከፍተኛ እውቅና ነው፡፡

መለስ በኢህአዴግ ውስጥ ኖረው በኢህአዴግ ውስጥ ያለፉ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡ በመንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችም ሆነ በተለያዩ የውጭ ታዛቢዎች በተደጋጋሚ እንደተነገረው የአገሪቱ የለውጥ ጎዳና የተደላደለ ሆኖ እንዲቀጥል የሚያስችለው አገራዊ የለውጥ ራዕይ በመለስ የአመራር ዘመን መሰረቱ ተጥሏል፡፡

እኚህን ታላቅ የአገር መሪ የፈጠረው ኢህአዴግ በውስጡ ሌሎች መለሶችም አሉ ብዬ እከራከራለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ የተፈጠረው እምነት፣ ተነሳሽነት፣ እልህና የመታደስ መንፈስ መለስን የወለደው ኢህአዴግ ያመጣቸው በዋጋ የማይተመኑ እሴቶች ናቸው፡፡ በእኔ አመለካከት ይህ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ሁሉም ጫፎች ዘልቆ እየሰፋ የመጣው ህዝባዊ ተቀባይነት በመለስ የአመራር ዘመን ለተጀመረው የህዳሴ ጉዞ መሳካት ከሚያስፈልጉት ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ነው፤ ይህን እውን ማድረግ

መቻሉ ብቻ ለገዢው ፓርቲ ከስኬቶች ሁሉ የላቀው ስኬት ነው የሚለው ፍፁም የማምንበት አመለካከቴ ነው፡፡

ምክንያቱም የመለስ ህልፈትን ተከትሎ በጥቂት አካላት የተናፈሰው፤ ከመናፈስም አልፎ በህዝቡ ውስጥ እንዲነሳ የተጎተጎተው አመፅና ስርዓት አልበኝነት ያለማንም መካሪና ጠባቂ ቦታ የተነፈገውና መና የቀረው የኢህአዴግና የመለስ አመራር በመላው ዜጋ ልብ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ በማግኘቱ ነው፡፡

አገሪቱን የሚመራው ድርጅት በዜጎች ዘንድ የዚህ ዓይነቱን ስፍራ ሊጎናፀፍ የቻለው ደግሞ ለአገርና ወገን አልኝታ የሆነ ጥንካሬን፣ ዴሞክራሲያዊነትንና ህዝባዊነትን የተላበሰ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ድርጅቱ የታነፀበት ባህሪ ደግሞ ለአሉባልታዎችና አፍራሽ አስተሳሰቦች በቀላሉ የማይሸነፍ ትውልድን መፍጠር ችሏል ብዬ አስባለሁ፡፡

እኔም ሆንኩ ማንም የአገራችንን ያለፉት ዓመታት የለውጥ ሂደት በአንክሮ የሚያጤን የመለስ ህልፈት እጅግ በሚያስቆጭ መልኩ የሚያጎድለው ነገር እንዳለ በእርግጠኝነት ይቀበላል፡፡

ሆኖም አገሪቱን የሚመራው ድርጅት ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ከመሆኑ አኳያ በመለስ መሪነት ተነድፎ ስራ ላይ እየዋለ የሚገኘው አገራዊ የለውጥ ራዕይ ተግባራዊ የሚደረገው  በሁሉም ዘርፍ የሚገኘው መንግስታዊ አመራርና ፈፃሚው አካል በጥልቀት መክሮበት፣ እውቀቱንና ክህሎቱን አክሎበት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

እኔ በታዘብኩት የኢህአዴግ የኖረ ባህል መሰረት ማናቸውም አገራዊ ጉዳዮች ከውሳኔ የሚደርሱት ብሎም ስራ ላይ የሚውሉት በየደረጃው የሚገኙት አካላቱ ጥልቅ ውይይት በማካሄድ ጉዳዩን ካበሰሉትና ጥልቀት ከሰጡት በኋላ ነው፡፡ ልማትን ጨምሮ ወደህዝቡ ዘልቀው እንዲመከርባቸው የሚደረጉ በርካታ አገራዊ ጉዳዮች መኖራቸውንም ብዙዎቻችን የምናውቅ ይመስለኛል፡፡

አገሪቱን የሚመራው ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊና አሳታፊ ባህልን የተላበሰ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ከመሪው የሚጠበቀው ሚና የላቀ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ለአገሪቱ እድገትና ለህዝቦቿ ተጠቃሚነት ታስበው የሚቀረፁት ውጥኖችም ሆኑ የሚወሰዱት እርምጃዎች አጠቃላይ የገዢው ፓርቲ ቁልፍ የአመራር አካላት እውቀትና ብስለት የሚታከልባቸው ናቸው፡፡

ኢህአዴግ ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከረ ሊመጣ የቻለበት ቁልፉ ሚስጥርም ይህ በጋራ ውይይትና ምክር ላይ የተመሰረተው የፖለቲካ አመራር ብሂሉ ነው፡፡ ይህ የአመራር ብሂሉ ነው ህዝባዊ ተአማኒነትንና ስኬትን ያቀዳጀው ብዬ አምናለሁ፡፡

ለዚህ ነው በመለስ የአመራር ዘመን መሰረቱ የተጣለው የህዳሴ ጉዞ በላቀ ትጋትና ተነሳሽነት ተጠናክሮ ይቀጥላል የምለው፡፡ በተለይ ከመለስ ህልፈት ጀምሮ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሪው ያሳየው ፍፁም ወገናዊነትና

አገራዊ ስሜት አገሪቱን ለሚመሩት ኢህአዴጎች የሚሰጠው የተለየ ትርጉም ከመለስ የላቀ መስዋእትነትን የሚጠይቅ ታላቅ ተግባርን ነው፡፡ ሰሞኑን ከተለያዩ የአገሪቱ መሪዎች የመናደምጣቸው መግለጫዎችና ቃል ኪዳኖች ደግሞ ይህንን የህዝብ አደራ ለመወጣት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

በአገሪቱ ዜጎች ልብ ውስጥ የተፈጠረው ጠንካራ መተማመን፣ አገራዊ መግባባትና የባለቤትነት ስሜት ደግሞ አገሪቱን የሚያስተዳድረው መንግስት የተጣለበትን የላቀ ኃላፊነት ለመወጣት ትልቅ ጉልበት ይሆናል፡፡ አገራችን ስትመኘው ለብዙ መቶ ዓመታት የኖረችውን ይህንን እጅግ ውድ የሆነ እሴት መቀዳጀት የቻልነው አገሪቱን የሚመራው ኢህአዴግ ከውልደቱ ጀምሮ እየተከተለው ባለው ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ አስተሳሰብ አማካኝነት በሁሉም ዘርፎች እያየናቸው ያሉትን አንፀባራቂ ለውጦች ተከትሎ ነው፡፡